# ጠ/ሚ ኣቢይ - ዳግማዊ ጎርባቸቭ ?

ሰሎሞን ገብረስላሴ

በ 21 ኛዉ ክፍለዘመን ከታዩት ተንሰራፍቶ የቆየን ስርአት የመለወጥ ሂደቶችና ሙከራዎች መካከል ኮሚኒዝምን የመለወጥ ማለትም  ወደ ተቃራኒዉ የካፒታሊዝም ስር አት የመለወጥ ሳይሆን ስብአዊነት እንዲላበስ የተደረጉ ሙከራዎች ታላቅ ስፍራ ይይዛሉ። ይህም ለዉጥ ያስፈለገዉ ካርል ማርክስ ሰዉ - በላ ያለዉ ካፒታሊስታዊ ስርአት በራሱ ቅራኔ ተተብትቦና ወድቆ፤ ሰብአዊነት የተላበሰ፤ ሰዉ በሰዉነቱ ብቻ የሚከበርበትና የማይበዘበዝበት፤ የምድር ገነት ይመጣል ያለዉ ትንቢት ወደ ተቃራኒዉ ሄዶ በሰራተኛዉ መደብ ስም የጥቂት ምርጦች አምባገነንነት በመስፈኑ ነዉ።

ለዉጡን ለማምጣት በዋነኛነት አንቀሳቃሽ የሆኑት ኮሚኒስት ፓርቲዉ ዉስጥ ካሉት መሪዎች የስርአቱን ብልሹነት ቀድመዉ ለማየት የቻሉ ናቸዉ። ጠ/ሚ አቢይን የወለዳቸዉ የህዝብ ትግል ነዉ የሚባለዉ 27 አመት ተንሰራፍቶ የቆየዉ የህወሃት አምባገነን አገዛዝ የፈጠራቸዉ ችግሮችና በነዚህ ችግሮች ላይ ያመጻዉ ዜጋ ነዉ። ችግሮቹ የሙብት ጥሰት፤ የኢትዮጵያዊነት መንቋቋሸሽ፤ የሙስና መንሰራፋት፤ አግላይና አድሎአዊ የብሄሮች ተጠቃሚነት፤ መግደል፤ ማሰር፤ ማሰቃየትና ማፈን መበራከት ወዘተ ናቸዉ። በኮሚኒስት ስርአት ዉስጥም ለዉጥ አራማጆችን የፈጠረዉ ነባራዊ ሁኔታ ስርአቱ የፈጠረዉ ኋላቀርነት፤ ለሰዉ ልጅ የሚያስፈልጉትን መሰረታዊ አቅርቦቶች ለሟሟላት አለመቻሉ፤የሙብት ረገጣዎች፤ የፓርቲ አመራር ምርጦች ምቹ ኑሮና የሰራተኛዉ ድህነት  ናቸዉ። በተለይም የተናቁትና ዘወትር የፕሮፓጋንዳ ዉርጂብኝ የሚደረግባቸዉ የካፒታሊስት ስርአት ተከታይ አገሮች የዜጎቻቸዉን የኑሮ ደረጃ እጅግ ማሻሻላቸዉና በምርምርና በፈጠራ ስራዎች ልቀዉ መገኘታቸዉ ቁጭት መፍጠሩ ነዉ። በተለይ ለሶቭየት ህብረት ደግሞ ከምእራቡ አለም ጋር በተደረገዉ ቀዝቃዛ ጦርነት ወታደራዊ ዉድድር የኑይክሌር ጦርነት አደጋ እየጨመረ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን፤ በአገሪቱ ባጀት ላይም ከፍተኛ ድቀት በማድረሱ በዚህ መልክ ለረጅም አመታት ለመቀጠል መቻሉን ለዉጥ አራማጆች በመጠራጠራቸዉ ነዉ።

ታላቅ ከሚባሉ የለዉጥ ሙከራዎች "የፕራግ ጸደይ" የሚባለዉ በቼኮዝሎቫኪያ በ 1968 እ.ኤ.አ የተሞከረዉ ለዉጥ ነዉ። በ አለክሳንደር ዱብቼክ የተመራዉ ይህ " የሰዉ ፊት ያለዉ ሶሽያሊዝምን" የማምጣት ጥረት ብዙ ሳይገፋ "ለምስራቅ አዉሮጳ ኮሚኒስት አገሮች ታላቅ ወንድም እኔ ነኝ" ባለዉ ሶቭየት ህብረት ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ሊከሽፍና የለዉጥ አራማጆች ሁሉ የተገደሉበት፤ የታሰሩበትና የተሰደዱበት ክስተት ነዉ። እርግጥ ከዚያ አንድ አስርተ አመት በፊት ባነሰም ደረጃ ቢሆን ተመሳሳይ ለዉጥ በሃንጋሪይ ተሞክሮ ተመሳሳይ እጣ ደርሶበት ነበር።

ለፕራግ ጸደይ ምናልባትም አነሳሽ የሆነዉ በ 20 ኛዉ የሶቭየት ህብረት ኮሚኒስት ፓርቲ አመራር ጉባኤ ላይ በ 1964 መሪዉ ክሩስቸቭ ተደፍሮ የማያዉቀዉን የስታሊንን አገዛዝ በተክለ ሰዉነት የተመራ ክፉ አገዛዝ ብሎ መናገሩና ሙሉ ለዉጥ ሳይሆን  በጥገናዊ ለዉጥ የፓርቲዉን የብቸኛ የአገዛዝ ሞኖፖል ለማስቀጠል ያደረገዉ ለሱም ከስልጣን መወገድ ምክንያት የሆነዉ ያልተሳካ ለዉጥ ሊሆን ይችላል።

ከዚህ በኋላ 20 አመት ጠብቆ በራሱ በታላቅ ወንድምየዉ አገር በሶቭየት ህብረት በጎርባቸቭ መሪነት የተከሰተዉ በ 1980 ዎቹ አጋማሽ አለምን ያስደመመ የሥር ነቀል ለዉጥ ሙከራና በመጨረሻም በታሰበዉ አቅጣጫ ያልሄደ ለዉጥ ነዉ። ጎርባቼቭ እንደ ጠ/ሚ አቢይ ወደ ስልጣን ሲመጡ የሚያማልሉ ንግግሮችን በማድረግ ከፍተኛ የህዝብ ተወዳጅነትን በአጭር ጊዜ አገኙ። እንዲያዉም ያሰቡትን ለዉጥ መርሃ ግብር ለመስጠትና ትርጉሙን በግልጽ ለማቅረብ "ፕሬስትሮካ" ና

"ግላስኖስት" የሚሉ ቅጽሎች ተጠቅመዉ ኮሚኒዝም ቅስሙን የሰበረዉን ህብረተሰብ ተሃድሶና የደከመዉን ኢኮኖሚ ማገገሚያና መፈወሻ መድሃኒቶችን አቀረቡ። እንደ ጠ/ሚ አቢይ የሶቭየት ክፍለሃገሮችን ተራ በተራ ጎበኙ። ከህዝቡ ጋር ተነጋገሩ። ችግሩን ለዋናዉ መሪ በቀጥታ ተናግሮ ለማያዉቅ ህዝብ እድል ሰጡ። መጀመሪያ ጉዟቸዉን በሌኒንግራድ (አቢይ በጂግጂጋ)፤ ቀጥሎ በተከታታይ በዩክሬይን (ትግራይ)፤ በምእራብ ሳይቤሪያ (አምቦ) በካዛኪስታን (ጎንደርና ባህር ዳር) ወዘተ ተንቀሳቀሱ።

እንደዛሬው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ አብዛኛዉ የሶቭየት ህብረት ህዝብም ተስፋ በተስፋ ተፍነሸነሸ፡ ብሩህ ቀናት ከፊቱ ታየዉ። ዛሬ ለ ጠ/ሚ አቢይ ዘፈን እንደተዘፈነላቸዉ ሁሉ፤ ጎርባቾቭም በአገር ዉስጥም በዉጭም በፍቅር መንፈስ "ጎርቢ" ጎርቢ ተባሉ። እንደሚገመተዉ ፓርቲዉ ዉስጥ የጎርባቾቭን ለዉጥ ከልብ የሚደግፉ ባንድ በኩል ሲቆሙ፤ ለዉጡ ለስልጣናቸዉ አደገኛ ጉዞ መሆኑን የተረዱት ከሁለት ጎራ ተከፈሉ። አንደኛዉ ወገን "እነሌኒንና ስታሊን ያቆዩልንን የኮሚኒዝም ቅርስ የሚያዋርድ ለዉጥ" ብለዉ በግልጽ ተቃዋሚዎች ሆኑ። ሁለተኛዉ ክፍል የሃይል ሚዛኑን በማየትና የህዝቡን የለዉጥ ፍላጎት በመፍራት አፋዊ ድጋፍ ለለዉጡ በጊዜያዊነት የሰጡ ነበሩ።

ገና 3 ወር ያልሞላዉን የ ጠ/ሚ አቢይ መንግስት፤ 6 አመት ሞልቶትና አሳዛኝ ዉጤቱ በግልጽ ታይቶ ካለፈዉ ስር አት ጋር ማነጻጸሩ በፍርድ ሚዛን ሲታይ ሙሉነት ይጎድለዋል። ሆኖም እንደሚባለዉ ብልህ ሰዉ ሌሎች ከሰሩት ስህተት ይማራል፤ ሰነፍ ሰዉ ሌሎች የሰሩትን ስህተት እያወቀም ይደግማል" ስለሚባል፤ የጠ/ሚ አቢይ መንግስት ከወዲሁ የጎርባቾቭን ስህተቶች (ራሳቸዉ ጎርባቾቭም ያመኗቸዉን) ማየት ስህተቱን ከመስራት ይታደገዋል።

ጎርባቾቭ ጠንቃቃና ንቁ ፖለቲከኛ መሆናቸዉ ሲያስመግናቸዉ ባንጻሩ እጅግ ጠንቃቃ እየሆኑ መምጣታቸዉ ወዳጆቻቸዉን አስከፋ። በማእከላዊ ኮሚቴ ያሉ ለዉጥ አራማጅ ወዳጆቻቸዉ ህዝቡ የሚፈልጋቸዉን ርምጃዎች በተከታታይ እንዲወስዱ ቢጎተጉቱም ጎርባቼቭ በሁለት ጎራ የቆሙትን ለዉጥ አጋቾች ላለማስቀየምና ላለማስከፋት ሲሉ ዉድ ጊዜ አባከኑ። አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን ስለ ጠ/ሚ አቢይ እንደሚያስበዉ ጎርባቾቭም ሰብአዊነት የተሞላቸዉ መሪ ስለነበሩ፤ የፖለቲካ አሻጥር የሚፈጽሙ መሪዎችን ወደ ስልጣን ማምጣት ቀጠሉ። ይህ በእጅጉ ወዳጆቻቸዉን አስከፋ። አልፎ ተርፎም ቅሬታዉ ወደ ህዝቡ ቀስ በቀስ መስፋፋት ጀመረ።

በዚህ ላይ በዴሞክራሲያዊ ለዉጡ ምክንያት ታፍኖ የነበረ ጎሰኝነት በግልጽ በአስቀያሚ መልኩ ወጣ።እዉነትን ያዘለዉም በዉሸት የተመሰረተዉም ቅሬታና ክስ እየተደበላለቀ በወሰን፤ በኗሪነት መብት ወዘተ የሶቭየት ህብረት ህዝቦች መተላለቅ ጀመሩ። የተደረገዉ የገበያ ኢኮኖሚ ብዙ ስር ስላልሰደደና የከሰሩ የመንግስት የኢኮኖሚ ተቋሞች እንደወትሮዉ በዉሸት የትርፋማነት ዘገባዎች በማቅረብ መቀጠል ስላልቻሉ ከስራቸዉ ብዙዎች ተባረሩ።

ምናልባትም ጠ/ሚ አቢይን በሚያስንቅ መልኩ ጎርባቾቭ በዉጭ አገሮች ጀግናና አንበሳ ተባሉ። የእንግሊዟ ታቼር አብረን ልንሰራዉ የምንችል ታላቅ መሪ አሏቸዉ። ሬጋንና ቡሽ የኑይክሌር አደጋን ለመቀነስ ጥሩ ሽሪክ አንዳገኙ ተረዱ። ጀርመን እንድትዋሃድ መሃንዲስ በመሆናቸዉ ሄልሙት ኮህል አደነቋቸዉ። በምስራቅ አዉሮጳም ታላቅ ወንድምነት ቀርቶ ሁሉም አገሮች የራሳቸዉን እድል እንዲወስኑ ለቀቋቸዉ። በሶቭየት ድጋፍ ጦርነት ሲያካሂዱ የነበሩ አገሮችም ርዳታዉ እንደሚቆም ተነገራቸዉ። አፍጋኒስታንና ኢትዮጵያ ትልቅ ቀዉስ ገጠማቸዉ።

"የዉጭ አልጋ፤ የቤት ቀጋ" እንደሆኑ በሚያስመስል መልክ አገራቸዉ ዉስጥ ግን ሁኔታዎች ከቁጥጥር ዉጭ እየሄዱ መጡ። መጀመሪያ 3 ቱ የቦልካን ክፍለሃገሮች ነጻነታቸዉን አወጁ። ብዙ ነጻነት በሚሰጠዉ የራስ ገዝነት እንዲቆዩ ቢለምኑ፤ ቢለምኑ አሻፈረን አሉ። ሌሎችም ክፍለሃገሮች በአድር ባይ መሪዎችና ስልጣን በታያቸዉ መሪዎች ግፊት ሶቭየት ህብረት ወደመበታተን ደረሰች። ለዚህ ምክንያት ዋነኛዉ የራሺያ ፕረዚደንት በኋላ የሆነዉ፤ በሰካራምነት የሚወቀሰዉ ባገሪቱ የዝርፊያ ካፒታሊዝም የመሰረተዉ የልትሲን ይገኝበታል።

ጠ/ሚ አቢይ ያገር መበታተን አደጋን በሚመለከት እንዲያዉም ከጎርባቸቭ በተቃራኒዉ ኢትዮጵያዊነትን በማንገስና ፓርቲያቸዉ ያዋረደዉን ስሟን በማደስ የሚመሰገኑ ሰዉ ናቸዉ። ርሳቸዉ ላይ እንደ ጎርባቸቭ የተጋረጠዉ አደጋ የለዉጥ ፈላጊዎችን እምነት ይዘዉ በመቀጠል ላይ ነዉ። ማስረጃዎቹ የሚያሳዩት ከላይ ባንድ ሰዉ ወይም በጥቂት ሰዎች በጎ ፈቃድ ብቻ የሚካሄድ ለዉጥ በህዝብና በተለያዩ ደሞክራሲያዊ ተቋሞች ድጋፍ ካልታጀበ ጽናት እንደማይኖረዉ ነዉ።ዴሞክራሲ በጸባዩ የህዝብ ተሳትፎ ነዉ። ነጻ ሚዲያ በቶሎ ተደራጅቶ ስራዉን ሲጀምር፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች የብሄራዊ መግባባት ዉይይቶች ሲጀመሩ፤ የደሞክራሲያዊና ስብአዊ ሙብቶች ታዉቀዉ ህዝቡ መንግስት እንዲፈጽምለት የሚፈልገዉን በሰለጠነ ሰላማዊ ሰልፍና በጽሁፍ ሲያስታዉቅ፤ በገለልተኛ አካል ባስቸኳይ ተጣርቶ የሙስና ጥልቀትና ስፋት ሲታወቅና ተጠርጣሪዎች የዘረፉትን ሲመልሱና ሰብ አዊ ሙብት የጣሱ በብሄራዊ እርቅ ክልል ለጥፋታቸዉ ተመጣጣኝ ቅጣት ከይቅርታ እሳቤ ጋር የሚሰጥበት ስርአት ባስቸኳይ ቢዘረጋ ለዉጡ በጥቂቶች ከመመራት ይልቅ በባለቤቱ ብዙሃን ይታቀፋል።

በ **90** ዎቹ መጀመሪያ ላይ፤ ጎርባቸቭ ወዳጆቻቸዉን አስቀይመዉ፤ ለተቃዋሚዎቻቸዉ ብርታት ሰጥተዉ፤ ለዉጡ የወለዳቸዉ ያልተጠበቁና የተጠበቁ ችግሮች ሁሉ እግር ተወርች ተብትበዋቸዉ፤ ያ በ **80** ዎቹ ኢጋማሽ የታየዉ ተስፋ እንደ ጉም በንኖ ብቻቸዉን ቤተሰባቸዉ ብቻ ከጎናቸዉ ቆሞ ማየት ታሪክ እንዴት መጸተኛ እንደሆነች ጉልህ ማስረጃዋን በማሳያነት ታቀርባቸዋለች። መፈንቅለ መንግስት በለዉጥ አጋቾች ተሞክሮባቸዉ ባይሳካም አይናቸዉ ፊት አገራቸዉ ፈርሳ የሚመሩት አገር ባለመኖሩ በቅጽበት ስልጣን አልባ የሆኑ የመጀመሪያዉ የአለማችን መሪ ሆነዋል።

ወፍራም ቆዳ ያላቸዉ መሪ በመሆናቸዉ ደግሞ አገራቸዉ ከፈረሰ ከ **5** አመት በኋላ ለራሽያ ፌደረሽን ፕረዚደንትነት ምርጫ ተወዳድረዉ በሚያሳዝን ሁኔታ **0.5%** ድምጽ ብቻ በማግኘት ወደፖለቲካ ፊታቸዉን ዳግም እንዳያዞሩ ታሪክ ፈረደች። የደረሰባቸዉን በደል በማጤን የጀርመኑ መሪ ኮህል ወደ ጀርመን መጥተዉ በሰላምና በክብር እንዲኖሩ የጋበዟቸዉን ሳይቀበሉ የፖለቲካ ጠላቶቻቸዉ (በተለይ ሰካራም የሚባለዉ የልትሲን) የክብር ጡረታ እንኳን እንዳይኖራቸዉ እግር በእግር በማዋረድ ከመኪና አቅም፤ ከቤት አቅም፤ ከጥበቃ አቅም ከልክሎ አቆራምዷቸዋል። እነሆ ዛሬ የ **87** አመት አዛዉንት የሆኑት ጎርባቼቭ ሚስታቸዉን ቀብረዉ ከልጃቸዉና ከልጅ ልጆቻቸዉ ጋር በአረጋዊነት ዘመን አለምን ይታዘባሉ።

እንደ ጠ/ሚ አቢይ ላለ መሪ ይህ የህዝብ ፍቅር ይህ የህዝብ ጭብጨባ ታላቅ እዳ የሚያስገባ ኩንትራት እንጂ ፤ በግብዝነት "ህዝብ ወዶኛል፤ የፈለገዉን ባላሟላለትም አሁንም ይወደኛል" የሚያስብል ሞቅታንና ራስን ማጃጃልን ሊያስከትል አይገባም። ይልቅስ ከታሪክ በመማር የህዝብ ፍቅር ሳይዉል ሳያድር ወደ ህዝብ ንቀትና ጥላቻ ሊለወጥ እንደሚችል ግምት ዉስጥ በማስገባት የለዉጥ ሃይሎችንና ራሱን ህዝቡን የለዉጡ ባለቤት በማድረግ የራስን ሚና እንደ ለዉጥ አዋላጅ በማየትና በመወሰን ታላቅ አገራዊ ዉለታ መስራት ይቻላል።

በተለይ ለዉጥ አጋቾችን ላለማስቀየም ሲባል የለዉጥ ሃይሎችን መጫን፤ አደጋዉ ከፍ ያለ እንደሆነ የጎርባቼቭ ታሪክ ምሳሌ ነዉ። ለዉጥ አጋቾች ምንም ጊዜ ከጥቅማቸዉ ዉጭ ለዉጡን የሚያዩበት አገራዊ መነጽር በአመዛኙ የላቸዉም። ለዉጥ አጋቾች ጠ/ሚ አቢይን ካስቸገሩና እንቅፋት ከደቀኑ ደግሞ ጠ/ሚ ይህን ሃቅ ለኢትዮጵያ ህዝብ በግልጽ አስታዉቀዉ ህዝቡ ለመሰረታዊ ለዉጥ የሚያደርገዉን ትግል ሳይዉል ሳያድር እንዲያጧጡፍ አገራዊ ጥሪ ሊያደርጉ ይገባል።

ግንቦት **2010**